# עבודות תלמידים

# የተማሪዎች የፈጠራ ሥራዎች

# የሕይወቴ ታሪክ በአጭሩ

ስሜ ፍቃዱ ይባላል። የተወለድኩት በጐንደር ክፍለ ሀገር በጭልጋ ወረዳ ሰራባ በምትባል ትንሽ ከተማ ነው። ጊዜውን በትክክል ባላውቀውም አብዛኛውን የልጅነት ሕይወቴን ያሳለፍኩት በሰው ቤት በመቀጠር ሲሆን ይኸውም በተለያዩ አካባቢዎች እየተዘዋወርኩ ከብት፥ ፍየል፥ አዝመራ በመጠበቅና ቤተሰቦቼን በመርዳት ነው። ለዚህም ዋና መንስዔው በልጅነታችን የአባታችን ማረፍና እናታችን ያለረዳት የቀረች ደሃ መሆን ነበር። ይሁን እንጂ ከዚህ በፊት ግን ለተወሰኑ ወራት መዋዕለ ሕጻናት ገብቼ ፊደላትን ቆጥሬ ነበር፤ ምንም እንኳ በቤተሰቡ የኢኮኖሚ ቀውስ የተነሣ ወዲያውኑ ባቋርጠውም።

በነዚህ በተወሰኑ ወራቶች ያሳለፍኳቸው የነጻነትና የልጅነት ጊዜያትን መቼም አልረሳቸውም። በተለይ ተናፋቂ የሕጻናት ጨዋታዎች እንደ አኩኩሉ፥ አብሮሽ፥ እቃቃ፥ መሐረሜን ያያችሁ፥ ወዘተ. እና ልዩ ጣዕምና ለዛ ያላቸው የሕጻናት መዝሙሮች ለምሳሌ "የልጅነት ጊዜ ጨዋታ፥ ሕጻኑ ማሙዬ፥ ከቤቴ በላይ ቁራ ሰፍሮ"፥ ወዘተ. ናቸው። በዚህም የተነሣ የመማር ልዩ ፍላጐት በሄድኩበትና በተቀመጥኩበት ሁሉ ቆራጣ ወረቀት ከእጄ አልተለየም ነበር።

ከላይ እንደገለጽኩት ብዙውን የልጅነት ጊዜዬን ያሳለፍኩት በሰው ቤት ስለሆነ በጣም ብዙ ስቃይና የሕይወት ገጠመኝ አይቻለሁ። በተለይ አብዛኛው የሰው ቤት ባህሎችና ለባዕድ ያላቸው አስተሳሰብ በሕይወቴ ውስጥ ትልቅ ጠባሳ ጥለው አልፈዋል። ከዚህ ሁሉ በኋላ በ12 ዓመቴ አንድ በጭራሽ ያላሰብኩትና ያልጠበቅኩት ወሬ ሰማሁ። ይኸውም በወላጆቼና በሽማግሌዎች የጭንቅላት ሳንዱቅ ውስጥ ተቆልፎ የነበረ፥ ከእነሱም ቅድመ አያቶች ሲወርድ ሲዋረድ በምስጢር የተላለፈ በጣም ምስጢራዊና በውስጡ የተስፋ ጭላንጭል ያለበት ልዩ ቃል "ኢየሩሳሌም" ነበር። መቼም ምንም እንኳን ስለኢየሩሳሌም ምንም ዕውቀት ባይኖረኝም በዚያን ጊዜ በወሬ ብቻ የተሰማኝ ደስታና ስሜት ገደብ አልነበረውም።

"ጉዞ ወደ ኢየሩሳሌም" በሚል መፈክር የአንድ አካባቢ ኗሪዎችና ቤተ ዘመዶች፥ ወጣቶች፥ ሽማግሌዎችና ሕጻናት በሙሉ ሳይቀር ያለን ሀብትና ንብረት በመሸጥ የተወለድንበት ቀዬና የአባቶቻችን ባድማ ትተን በአውቶቡስ ወደ አዲስ አበባ ጉዞ ጀመርን። በጉዞአችን በጣም ብዙ ችግሮችና ገጠመኞችን አሳልፈናል። ይኸውም ለኛ መንገዱ ጨርሶ እንግዳ ነበር። በኋላ ግን እንዳይደረስ የለም አዲስ አበባ በሰላም በሕይወት ገባን። ይኸውም የሕይወታችን የመጀመሪያ ጉዞ ነበር።

በመጨረሻ አዲስ አበባ ውስጥ መገናኛ በሚባል ሰፈር ውስጥ ቤት 80 ብር ለወር ተከራይተን በናኮጅ (NACOEJ) እና በጆዲሲ (JDC) ረጂነት ልጆች እየሠሩ ከፊሎች ደግሞ ዝም ብለው በአዲስ አበባ ኑሮ ውድነት እየተሰቃየን ለ7 ዓመት ተቀመጥን። በነዚህ ዓመታት ብዙ ችግሮች የገጠመኝ ሲሆን ጥሩ ነገርም አግኝቻለሁ። ለምሳሌ ከ1ኛ እስከ 6ኛ ክፍል ድረስ ትምህርቴን በአመርቂና በአኩሪ ውጤት ተከታትያለሁ፣

የትምህርትን (የዕውቀትን) ጣዕምና ጥቅም በሚገባ ተረድቻለሁ። ይኸን ያህል ጊዜ ስንቆይ “የሚቀጥለው ዓመት በግዚአብሔር እርዳታ በኢየሩሳሌም” በማለት ነው። በዚህም የተነሣ በጽኑ ትእግሥታችንና በብርቱ ተስፋችን በማያቋርጥ ጸሎታችን ከ7 ዓመት ኑሮ በኋላ በእግዚአብሐር እርዳታ ወደ እስራኤል በአውሮፕላን ተሳፍረን “ቤን ጉሪዮን” ከሚባለው የእስራኤል አየር ማረፊያ ተራገፍን። ይህቺም ዕለት ባልሳሳት እንደ ኤውሮፓውያን አቆጣጠር በ25.5. 2004 ሰኞ ጧት በ9 ሰዓት ነበር። በዚህች ቅዱስና የብዙ ዓመት የሕልሜ ዕውነታ የተፈጸመበት ቀን የተሰማኝ ደስታ በሕይወቴ በጣም ትልቅ ነበር።

ከዚያም በአስተባባሪዎች (ማድሪኾች) አማካይነት በቤርሼቫ ከተማ ወደሚገኘው ኑሪት መርካዝ ቅሊጣ ተወሰድን። ጊዜያዊ መኖሪያ ቤትም ተቀበልን። በሳምንቱም እኔ ወደ ክፋር ሳባ “ኡልፓን ሳፒር” ተወስጄ ለ10 ወራት ያህል የዕብራይስጥን ቋንቋ ተማርኩኝ። በነዚህ ወራት እንኳንስ ዕብራይስጥ ልናገር ለመስማትም አልሜና አስቤ ስለማላውቅ ማውራትና መረዳት ለእኔ የሕይወቴ የመጀመሪያ እርምጃ ነበር። ይህ ብቻ አይደለም። በኡልፓን ስለእስራኤል ሀገር በጉብኝት መልክ ብዙ ዕውቀቶችን ገብይቻለሁ። በአጭሩ ኡልፓን ለእኔ ለእስራኤል ሀገር ዋና መክፈቻ ቁልፍ ነው። ይኸውም ከኅብረተሰቦቿ ጋርና ከቴክኖሎጂ ጋር ለመዋሃድ በመጠኑ ረድቶኛል።

በሰው ሕይወት ውስጥ ሁሉም ወደፊት መራመድ አለና እኔም በእስራኤል ሕግና ደንብ መሠረት በኡልፓን ውስጥ ሃይማኖትና ሌሎች ሥነ ሥርዓቶችን አሟልቼ ወደ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ለመግባት ወደ ሰሜናዊ የሀገሪቱ ክፍል ተወስጄ አፉላ አጠገብ “ኒር ሃኤሜክ” በሚባል ገጠር በመስፈር በኤሜክ ይዝራኤል ኮሌጅ የቅድመ ዝግጅት ትምህርቴን በመከታተል ለሁለት ዓመት ቋሚ የትምህርት ፕሮግራም አለፍኩ። በዚህ ሰዓት በመጀመሪያ ዓመት የአማርኛ፣፣ የሒሳብና የእንግሊዝኛ ባግሩት ፈተና ለማድረግ በዝጅት ላይ እገኛለሁ።

ከትምህርትና ከፈተና በኋላ በአምላክ ፈቃድ በሀገሪቱ ሕግ መሠረት ወደ ውትድርና በመሄድ ግዴታዬን በሚገባ ለመወጣት ዕቅድ ያለኝ ሲሆን የወደፊት ዓላማዬ በአጭሩ ከውትድርና ተመልሼ፥ ሥራ ሠርቼ ብር ካጠራቀምኩ በኋላ የተወለድኩባትንና ያደግኩባትን ሀገሬን ኢትዮጵያን ማየትና ከዚያም ተመልሼ በመማር እስራኤል ሀገር ጐልቶና ተስፋፍቶ የሚገኘውን የወገኔን ችግር ለመቅረፍ የበኩሌንና የተቻለኝን ጥረት ማድረግ ችግሮች የሚፈቱበት ዋና መንገድ ፈልጐ እልባት ማስገኘት ነው።

ከእግዚአብሔር እርዳታ ጋር